# ሰውየው ይቃዣሉ ልበል?

ሰውየው ያልኩት ያው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ነው። መቼም ጆሮ የማይሰማው ነገር የለም፡ ሰሞኑን ደግሞ ድህነት እየተረገመ ነው። በአንድ ወቅት እድገታችን ሁለት ዲጂት ነው እየተባለ በሌለ እድገት ሲፎለል ተከረመ። መብራት በመላው ሐገሪቷ ላይ በሳምንት እስከ አራት ቀን ሲጠፋ እና አቅርቦቱን ማሻሻል የማይታሰብ ሲሆን ይህንን ችግር ያመጣው ያው እድገታችን በከፍተኛ ፍጥነት በመሆኑ ልንቋቋመው ባለመቻላችን ነው እየተባለ ድክመትን አቅምን ያለማወቅ ተረት ተረት ሲነገረን ከረመ። አሁን ደግሞ ሰሞኑን፣ በዛ በማስመሰያ ፓርላማ ሰውየው አሁን ለመጣብን ችግር ተጠያቂው “ድህነት” ነው ብለው ተናገሩ አሉ። ይቃዣሉ ወይ ያልኩት ለዚህ ነው፡ የቱ ድህነት? ድህነት ተረት የሆነ መሰሎኝ። አሁንም አለ እንዴ? ሁለት ዲጂት ኢኮኖሚው እያደገ፡ ምርት ጨምሮ የምን ድህነት ነው የሚያወሩት?

አንድ ጊዜ እኚሁ ሰውዬ በዚሁ አስቂኝ የፓርላማ ትርኢት ሲደመጡ ከ6.4ቱ ሚሊዮን የምግብ እጥረት ከደረሰበት ህብረተሰብ በስተቀር (አስቡ እዚህ ላይ ረሃብ አይደለም የምግብ እጥረት ነው ነገሩን ቀለል ለማድረግ፣ 6.4ሚሊዮን ምን አላት) ሌላው ከ70ሚሊዮን በላይ የሚሆነው ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን ኑሮው የተሻሻለ መሆኑን ከተናገሩ ጊዜው ሩቅ አልነበረም። ያች ቃል ሳትረሳ አሁን ደግሞ ለዚህ ውድቀት የዳረገን ድህነት ነው ተብሎ ክስ ቀረበበት። መቼ ይሆን ይህ ሁሉ ውሸት የሚያበቃው? በሕዝብ ላይ መሳቁና መሳለቁ የሚያከትመው? ጊዜው ሩቅ የሚሆን አይመስለኝም።

በምእራባውያኑ አገሮች እንደልምድ የሚታየው አንድ ሰው ሥራውን መሥራት ካልቻለ በቂ አይደለሁም ብሎ በፍቃደኛነት ስራውን መልቀቅ ልክ እንደ አንድ ባህል ነው። የኛዎቹ ግን መሥራት ሲያቅታቸውና እርስ በርስ ለመሸፋፈን ይመስላል ምንም የማይናገረው ድህነት ተጠያቂ ነው ተብሏል። አሁንስ ጥርሴስ ልማዱ ነው ምኔን አታስቀው!! አለ አንዱ ሲተርት።

ከወላጅ እናቴ ጋር ስናወራ ያው ኢኮኖሚው ሁሌም አነዱ ዋነኛ አርስት ነው፡ ይሄ ተወደደ ይሄም ዋጋው ከፍ አለ፡ ይሄማ ከሐገሩ ጠፍቷል፣ መብራት የለንም በጭለማ ነው ቁጭ ያልነው ወዘተ... እያለች ሁሉንም በዝርዝር ሳትነግረኝ አታልፍም። አንድ ቀን ታዲያ እንደለመደችው ያለውን ችግር ስትዘረዝር፣ ለዚህ ሁሉ እኮ ድህነት ነው ተጠያቂው ስላት፣ እሱን እነኳን ተወው፡ ዛሬ ገበሬው እንኳን ሀብታም በሆነበት ወቅት የምን ድህነት ነው የምታወራው ብላ በስላቅ ትነግረኛለች፡ እንዴት ስላት፡ ማታ ማታ አለችኝ፡ ማታ ማታ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ስሙ ነው እንጂ ቲቪውም የነሱ ነው) አንዱን ገበሬ የማን ቪላ ውስጥ አስገብተው እነደሆነ አላውቅም አሁን ሀብታም ነኝ ኑሮዬ ተሻሽሏል፣ ቤት አለኝ ገንዘብ አለኝ እድሜና ጤና ለፀሐዩ መንግስታችን እያለ ያከማቸውን የገንዘብ መጠን በሚሊዮን ይናገራል። ሚሊዮን ቁጥር መሆኑን ያውቅ እንደሆነ ነው እነጂ ገንዘብስ በመቶም ቆጥሮ የሚያውቅ አይመስልም እኮ ስታየው! አሁንስ የኔ ልጅ በቃ ምንም እንደማያውቅ እንስሳ ነው የቆጠሩን፤ ወይም ሊያታልሉን የሚሞክሩት፡ ልክ እንደ ህፃን ልጅ ነው፣ ከምንም አልቆጠሩን እኮ ትለኛለች።

እሺ ድህነትስ ተጠያቂነቱን ተቀበለ እንበል፡ እናስ? ቃሊቲ ወርዶ ቁጭ ብሎ የማይሆን ስዕል ሲስል እየሳለ ሊቀመጥ? (በነገራችን ላይ ሰዕል ስል አነድ ነገር ትዝ አለኝ፡ የቀድሞው የ “ፍትህ” ሚኒስትር አሰፋ ቀሲቶ የፍትህ ያለ በማለት እየጬኹ ነው አሉ፡ ነገሩ እንዲህ ነው፣ ከፍትህ ሚኒስትርነታቸው ከተነሱ በኋላ በድሮው ቤታቸው ሲኖሩ ሳለ አሁን በቅርቡ የቤት ኪራይ ውዝፍ እዳ ተቆልሎ ይመጣባቸዋል፡ እናም በ10 ቀን ውስጥ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ ይሰጣላቸዋል፡ በዛም ምክንያት ከሚኖሩበት ቤት ይወጣሉ፡ እናም ምን አሉ፣ የወጣሁት በውሳኔው አምኜ ሳይሆን ታስሬ የማይሆን ስዕል ከመሳል ብዬ ነው) ወደ ዋናው ሃሳቤ ልመለስ እና ከዚያም ድህነት የተለመደው የካንጋሮ ፍርድ ቤት በቀጠሮ ሊመላለስ? ለክሱ እንዲሆኑ

የተፈበረኩ አስቂኝ መረጃዎች እና የተነገራቸውን በደንብ አጥንተው ባልመጡና በተከፈላቸው ምስክሮች የሆነው ያልሆነው ሊቀባጠር? አንቀፅ ሊመዘዝ? ይህ ሁሉ ሊደረግ?

እንደሚመስለኝ ሰውዬው ዝም ብለው ያላዩትን ነው የሚናገሩት፡ የትኛውን ገበሬ ሄደው አነጋግረው አይተው ነው የኑሮውን መሻሻል ያዩት? የከተማው ሰው እንኳን በቴሌቪዥን ካለሆነ አያውቃቸውም፡ ደፍረው ወጥተው ከሰው ጋር የሚገናኙበት ጊዜም ኖሮም ስለማያውቅ ከሕዝብ ጋር እንደ ሕዝብ መሪ ለመነጋገር ድፍረቱም ኖሯቸው አያውቅም። በእውነት የናፈቀኝ ምን መሰላችሁ፡ በኢትዮጵያ መሪ ተብሎ የተቀመጠ ሕዝቡን የሚያውቅ፣ ሕዝብ የተሰበሰበበት ቦታ ወጥቶ ከሕዝብ ጋር እጅ ለእጅ የሚጨባበጥ ሕዝብን የሚያነጋግር መሪ። በእውነት የሌሎች ሐገሮች መሪዎች ይህንን ሲያደርጉ ሳይ መቼ ነው የኛዎቹ የዚህን አይነት ድፍረት የሚኖራቸው እላለሁ። ግን እውነተኛ የሆነ፣ ኮሮጆ ያልገለበጠ፣ በሕዝብ የተመረጠ መሪ ሥልጣን ላይ እስካልወጣ ድረስ መሪዎቻችን ጓዳ ለጓዳ ነው እንጂ ደፍረው ለመታየት አይሞክሩም።

እናም ሰውየው በአማካሪዎቻቸው የሚቀርብላቸውን ነው ዝም ብለው የሚያነበንቡት፡ የሕዝቡን ችግርና የሰቆቃ ኑሮ ግን የሚያውቀው በውስጡ የሚኖረው ሕዝብ ነው። በሰውዬው ሁኔታ በሚቀጥለው ንግግራቸው እድገታችን ሦስት ዲጂት ነው ቢሉ አይገርመኝም ሁሌም የሌለ ነገር ነውና የሚወራው። ነገር ግን አቅምን ማወቅና ለደረሱት ድክመቶች ተጠያቂ የሚሆኑትን ለይቶ በማውጣት ድክመታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ አሊያም በሌሎች ውጤት ለማምጣት ሊሰሩ በሚችሉ መተካት ያሉትን ሁኔታዎች ሊቀይር ይችላል። አለዚያ አደገ አደገ የምንለው ኢኮኖሚያችን ለሕዝባችን የሕልም እንጀራ ከመሆን በቀር የትም አያደርሰንም። በሐገራችን ብሔራዊ እርቅ ተደርጎ ሁሉም እርስ በርሱ በመቻቻልና በሠላም ለመኖር ቃል ገብቶ ሐገሩን ለቆ ለመውጣት ያሰበው ምሑር ባላበት እንዲቆይ፡ ውጭ ወጥቶም ሌላውን ባእድ ሐገር በማልማት ላይ የሚገኘው ምሑርም ወደ ሐገሩ ገብቶ፣ ሁሉም ጉልበቱንም ሆነ እውቀቱን ለሐገር እድገት በማዋል ሐገራችን ኢትዮጵያ የጎደፈና የተዋረደ ስሟ የሚለወጥበትን ጊዜ አምላካችን እንዲያቀርብልን ይርዳን።

ሠላምና ፍቅር ያድለን

ፍቅሩ ይበልጣል ነኝ ከዩኬ